جمعية خدمة المحتوى
الإسلامي باللغات

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com



# የጉዞ ስነስርዓትና ህግጋቶቹ

አማርኛ

أمهري

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

شركاء التنفيذ :

دار الإسلام | بيان الإسلام | رواد الترجمة | المحتوى الإسلامي

يتاح طباعة هذا الإصدار ونشره بأي وسيلة مع الالتزام بالإشارة إلى المصدر وعدم التغيير في النص

Tel : +966 50 244 7000
info@islamiccontent.org
Riyadh 13245-2836
www.islamiccontent.org

# የጉዞ ስነስርዓትና ህግጋቶቹ

ምስጋና የአለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ነው። ሶላትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ላይ ሁሉ ይስፈን። በመቀጠልም፡-

ይህ የጉዞ ስነስርዓትና ህግጋትን በተመለከተ የሚያትት አጠር ያለ መልዕክት ነው። አንድ ተጓዥ አብዛኛው ጊዜ የሚያስፈልጉትን ጉዳዮች ለማብራራትም ጥረት አድርገናል።

አላህን ብቻ ለተከበረው ፊቱ ጥርት ተደርጎ የተዘጋጀ እንዲያደርግልንና ለመላው ሙስሊሙ ማህበረሰብ ጠቃሚ እንዲያደርግልን እንጠይቀዋለን።

የእስላማዊ አስተምህሮቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች አገልግሎት ማህበር የዕውቀት ዘርፍ ኮሚቴ

# የመጀመሪያው፡ የጉዞ ስነስርዓት

ሐጅ ለማድረግ ወይም ለሌላ አምልኮዎች ጉዞ የሚያደርግ ሰው የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል፡

1

**የሐጅና ዑምራ ጉዞዎች ቅዱስ ጉዞዎች ስለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ቢሆንም ስለሚሄድበት ወቅት፣ መጓጓዣ፣ ስለሚያካሂደው ጓደኛ፣ ወዳሰበው ቦታ የሚወሰዱ በርካታ መንገዶች ካሉ ስለሚሄድበት የመንገድ አቅጣጫ (ሰግዶ) የላቀውን አላህን ያማክር። የእውቀትና የመልካም ባለቤት የሆኑን ሰዎችንም በዚህ ጉዳይ ያማክር።**

አላህን የሚያማክርበት ሁኔታ አፈፃፀሙም፡ ሁለት ረከዓ ይሰግዳል ቀጥሎ ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) የመጣውን ዱዓ ያደርጋል።



2

**ሐጅና ዑምራ የሚያደርግ ሰው በሐጁና በዑምራው የላቀውን የአላህን ፊት ማሰቡና ወደርሱ መቃረብን ማሰቡ ግዴታ ነው። እንዲሁም የዱንያን ሰባሪ ጥቅም ከማሰብ ወይም ፋኪራን ከማሰብ ወይም (ሐጅ እገሌ መባልን የመሰለ) ቅጥያ ስም ማግኘትን ከማሰብ ወይም ይዩልኝና ይስሙልኝን ከማሰብ መጠንቀቅ ይገባዋል።**

ይህ ስራው እንዲበላሽና ተቀባይነት እንዲያጣ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነውና።

**የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል:**

﴿قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَىَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ فَمَن كَانَ يَرْجُوا۟ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَٰلِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدًۢا﴾

{«እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ። የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው።}

[አልከህፍ:110] በሐዲሠል ቁድሲይም እንደተላለፈው:

«أَنَا أَغْنَى الشُّرَكَاءِ عَنِ الشِّرْكِ، مَنْ عَمِلَ عَمَلًا أَشْرَكَ فِيهِ مَعِي غَيْرِي تَرَكْتُهُ وَشِرْكَهُ».

**("እኔ በሽርክና ከመጋራት ከተብቃቁ ሁሉ እጅግ የተብቃቃሁ ነኝ። አንድን ሥራ ሠርቶ በውስጡ ከእኔ ጋር ሌላን አካል ያጋራ እንደሆነ እርሱንም ሆነ የሽርክ ተግባሩን እተዋዋለሁ።")[1]**



(1) ሙስሊም በቁጥር (2985) ዘግበውታል

## 3

**የሐጅና ዑምራን ጉዞ የሚጓዝ ሰው መፈፀሙ ግዴታ የሆነበትን ነገር እንዳይተው ወይም ክልክል የሆነበትን ነገር እንዳይፈፅም ከመጓዙ በፊት የዑምራና የሐጅን ህግጋትንና የጉዞ ህግጋትን መገንዘብ ይገባዋል።**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦

«مَنْ يُرِدِ اللهُ بِهِ خَيْرًا يُفَقِّهْهُ فِي الدِّينِ» .

**(አላህ መልካም ለሻለት ሰው ሃይማኖቱን ያስገነዝበዋል።)**[2]

## 4

**የሐጅ ወይም የዑምራ ጉዞ የሚያደርግ ሰው ለሐጁና ዑምራው ሐላል የሆነ ገንዘብን መምረጥ አለበት። ምክንያቱም አላህ መልካም ነው ከመልካም ውጪም አይቀበልም።**

በተጨማሪም ሐራም የሆነ ገንዘብ የዱዓን ተቀባይነት የሚያሳጣ አንዱ ምክንያት ነውና።

## 5

**ከሁሉም ወንጀሎችና ሐጢዓቶች ተውበት ማድረግ፤ ገንዘብ ነክም ይሁን ክብር ነክ ወይም ከዛ ውጪ ባሉ ጉዳዮች ሰዎች ላይ የሰራው ግፍ ካለ መመለስና ይቅርታቸውን መጠየቅ ይኖርበታል።**

## 6

**አንድ ጉዞ የሚወጣ ሰው፤ ሰው ዘንድ ያለውንም ሰው ላይ ያለበትንም ኑዛዜውን መጻፉ ይወደድለታል።**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል:

«مَا حَقُّ امْرِئٍ مُسْلِمٍ لَهُ شَيْءٌ يُوصِي فِيهِ يَبِيتُ لَيْلَتَيْنِ إِلَّا وَوَصِيَّتُهُ مَكْتُوبَةٌ عِنْدَهُ» .

**(የሚናዘዘው ነገር ያለው ማንኛውም ሙስሊም፤ ኑዛዜውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ እርሱ ዘንድ ሳያስቀምጥ ሁለት ሌሊት እንኳ ማደር ተገቢ አይደለም።)**[3]

---

(2) ቡኻሪ በቁጥር (2738) እና ሙስሊም በቁጥር (1627) ዘግበውታል
(3)አቡ ዳውድ በቁጥር (4833) ዘግበውታል

ኑዛዜውንም በሰዎች ያስመስክር፤ በርሱ ላይ ያሉበትን እዳዎችንም ይክፈል፤ እርሱ ዘንድ የተቀመጡ አደራዎችንም ወይ ለባለቤቶቻቸው ይመልስ ወይም ደሞ እርሱ ዘንድ እንዲቆይ ያስፈቅዳቸው።

## 7

## አንድ ጉዞ የሚወጣ ሰው ለጉዞው መልካም ጓደኛ መምረጡ ይወደድለታል። የሚመርጠው ጓደኛ የሸሪዓ ዕውቀት ፈላጊ እንዲሆን ጥረት ያድርግ።

ይህም ጉዞው ላይ፣ ሐጁ ላይና ዑምራው ላይ ለስህተት እንዳይጋለጥና መልካሙን እንዲገጠም ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው:

«الرَّجُلُ عَلَى دِينِ خَلِيلِهِ، فَلْيَنْظُرْ أَحَدُكُمْ مَنْ يُخَالِلُ»؛

**"ሰውዬው በጓደኛው ሃይማኖት ላይ ነውና እያንዳንዳችሁ የሚጎዳኘውን ሰው ይመልከት።"[4]**

በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህም ብለዋል:

«لَا تُصَاحِبْ إِلَّا مُؤْمِنًا، وَلَا يَأْكُلْ طَعَامَكَ إِلَّا تَقِيٌّ».

**(ከአማኝ በቀር አትጎዳኝ፤ አላህን ከሚፈራ ሰው በቀር ምግብህን አይብላ።)[5]**



(4) አቡ ዳውድ በቁጥር (4832) ቲርሚዚይም በቁጥር (2395) ዘግበውታል
(5) ጦበራኒይ በቁጥር (823) ዘግበውታል



## 8

## ተጓዥ የሆነ ሰው ቤተሰቡን፣ ቅርብ ዘመዶቹን፣ ጎረቤቶቹንና ባልደረቦቹን መሰናበት ይወደድለታል። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) እንዲህ ብለዋል:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) እንዲህ ብለዋል:

«مَنْ أَرَادَ أَنْ يُسَافِرَ فَلْيَقُلْ لِمَنْ يُخَلِّفُ: أَسْتَوْدِعُكُمُ اللهَ الَّذِي لَا يُضِيعُ وَدَائِعَهُ»،

**«ጉዞ መውጣት የፈለገ ሰው ትቷቸው ለሚሄዳቸው እንዲህ ይበል: "አስተውዲዑኩሙሏህ አለዚ ላዩዲዑ ወዳኢዐሁ"» [ትርጉሙም: እናንተን (እንዲጠብቃችሁ) አደራውን ለማያጠፋው አላህ አደራ እስጠዋለሁ።]** (6)

ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ባልደረቦች መካከል አንዱ ጉዞ መውጣት በፈለገ ጊዜም እርሳቸው እንዲህ በማለት ይሰናበቱት ነበር:

«أَسْتَوْدِعُ اللهَ دِينَكَ وَأَمَانَتَكَ وَخَوَاتِيمَ عَمَلِكَ»،

«አስተውዲዑሏሃ ዲነክ ወአማነተክ ወኸዋቲመ ዐመሊክ» (ትርጉሙም: ሃይማኖትህን፣ እምነትህንና የስራህን ፍፃሜ ለአላህ አደራ እስጠዋለሁ።) (7)

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ጉዞ ከሚወጡ ሰዎች መካከል ከርሳቸው ምክር ፈልጎ ለሚመጣ ሰው እንዲህ ይሉ ነበር:

«زَوَّدَكَ اللهُ التَّقْوَى، وَغَفَرَ ذَنْبَكَ، وَيَسَّرَ لَكَ الخَيْرَ حَيْثُ مَا كُنْتَ»

«ዘወደከሏሁ ተቅዋ ወገፈረ ዘንበክ ወየሰረ ለከ አል-ኸይረ ሐይሡ ማኩንተ» (ትርጉሙም: አላህ ፍራቻውን ያሰስንቅህ፤ ወንጀልህንም ይማርልህ፤ የትም ሆነህ መልካምን ያግራልህ።) (8)

---

(6) ኢማሙ አሕመድ በሙስነዳቸው በቁጥር (4524) ዘግበውታል

(7) ቲርሚዚይ በቁጥር (3444) ዘግበውታል

(8) ኢማሙ አሕመድ በሙስነዳቸው በቁጥር (9724) ዘግበውታል

አንድ ጉዞ መውጣት የፈለገ ሰውዬ ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመምጣት "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምከሩኝ" አለ፤ እርሳቸውም:

«أُوصِيكَ بِتَقْوَى اللهِ، وَالتَّكْبِيرِ عَلَى كُلِّ شَرَفٍ» فَلَمَّا مَضَى قَالَ: « اللَّهُمَّ ازْوِ لَهُ الْأَرْضَ، وَهَوِّنْ عَلَيْهِ السَّفَرَ» .

**("አላህን በመፍራትና በየሁሉም ከፍታ ላይ ስትወጣ ተክቢራ (አላሁ አክበር) እንድትል እመክርሃለሁ።" አሉት። በሄደም ጊዜ "አላህ ሆይ! መሬትን ሰብስብለት (አሳጥርለት) ጉዞውንም አቅልልለት" አሉ።)**[9]

## 9

### ጉዞ ሲወጣ ከራሱ ጋር ቃጭል፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችና ውሻ አብሮ አይያዝ።

ይህም አቡ ሁረይራ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) ባስተላለፉት ሐዲሥ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሰላሉ ነው:

«لَا تَصْحَبُ الْمَلَائِكَةُ رُفْقَةً فِيهَا كَلْبٌ وَلَا جَرَسٌ» .

**(መላእክቶች ውሻም ይሁን ቃጭል ያለበትን ጉዞ አይጎዳኙም።)**[10]



(9) ሙስሊም በቁጥር (2113) ዘግበውታል

(10) ቡኻሪ በቁጥር (2593) እና ሙስሊም በቁጥር (2770) ዘግበውታል

## 10

ከአንድ በላይ ሚስቶች ኑረውት ለጉዞ አንዷን ብቻ ይዞ መውጣት ከፈለገ በመካከላቸው እጣ ይጥላል። እጣው የደረሳት ማንኛዋም ሚስቱ አብራው ወደ ጉዞው ትሄዳለች።

ይህም ዓኢሻህ (አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና) እንዲህ ስላለች ነው:

«كَانَ رَسُولُ اللهِ صلى الله عليه وسلم: إِذَا أَرَادَ سَفَرًا أَقْرَعَ بَيْنَ نِسَائِهِ، فَأَيَّتُهُنَّ خَرَجَ سَهْمُهَا خَرَجَ بِهَا مَعَهُ».

«የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጉዞ መውጣት የፈለጉ ጊዜ በባለቤቶቻቸው መካከል እጣ ይጥሉ ነበር። እጣ የደረሳት ማንኛዋም ባለቤታቸው ከርሳቸው ጋር አብራ ለጉዞ ትወጣ ነበር።»(11)

## 11

ከተቻለ ለጉዞ የሚወጣው ሀሙስ እለት በቀኑ መጀመሪያ ላይ ቢሆን ይወደድለታል።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለፈፀሙት ነው። ከዕብ ቢን ማሊክ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ:

«لَقَلَّمَا كَانَ رَسُولُ اللهِ صلى الله عليه وسلم يَخْرُجُ إِذَا خَرَجَ فِي سَفَرٍ إِلَّا يَوْمَ الْخَمِيسِ».

«የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሐሙስ ቀን በስተቀር በሌላ ቀን ለጉዞ እምብዛም አይወጡም ነበር።»(12)

## 12

ለጉዞም ይሁን ከዛ ውጪ ወደ ሆነ ቦታ ሲወጣ ከቤት ሲወጣ የሚባለውን ዱዓ ማድረጉ ይወደድለታል:

ሲወጣ እንዲህ ይላል:

(11) ቡኻሪ በቁጥር (2949) ዘግበውታል
(12) አቡ ዳውድ በቁጥር (5094) ዘግበውታል

«بِسْمِ اللهِّ، تَوَكَّلْتُ عَلَى اللهِ، وَلا حَوْلَ وَلا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ، اللَّهمَّ إِنِّي أَعوذُ بِكَ أَنْ أَضِلَّ أَوْ أُضَلَّ، أَوْ أَزِلَّ أَوْ أُزَلَّ، أَوْ أَظْلِمَ أَوْ أُظْلَمَ، أَوْ أَجْهَلَ أَوْ يُجْهَلَ عَلَيَّ» .

(ቢስሚላሂ ተወከልቱ ዐለላሂ፤ ወላ ሐውለ ወላቁወተ ኢላ ቢላህ፤ አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ አን አዲለ አው ኡደለ አው አዚለ አው ኡዘለ አው አዝሊመ አው ኡዝለመ አው አጅሀለ አው ዩጅሀለ ዐለየ) ትርጉሙም (በአላህ ስም በአላህ ላይ ተመክቼ እወጣለሁ። ኃይልም ይሁን ብልሃት በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በቀር የለም። አላህ ሆይ! እኔ ከመጥመም ወይም ከማጥመም ወይም ወንጀል ላይ ከመውደቅ ወይም ሌላን ወንጀል ላይ ከመጣል ወይም ከመበደል ወይም ከመብበደል ወይም የመሃይማን ስራ ከመስራት ወይም የመሃይማን ስራ እኔ ላይ ከሚሰራብኝ ባንተ እጠበቃለሁ።) ማለት ነው። (13)

## 13 እንስሳውን ወይም መኪናውን ወይም ፕሌኑን ወይም ከዛ ውጪ ባሉ መሳፈሪያዎች ላይ ሲሳፈር እንዲህ ብሎ የጉዞን ዱዓ ማድረጉም ይወደድለታል:

«اللهُّ أَكْبَرُ، اللهُّ أَكْبَرُ، اللهُّ أَكْبَرُ ثُمَّ يَقُولُ: {سُبْحَانَ الَّذِي سَخَّرَ لَنَا هَذَا وَمَا كُنَّا لَهُ مُقْرِنِينَ وَإِنَّا إِلَى رَبِّنَا لَمُنْقَلِبُونَ} [الزخرف: ١٤] اللَّهُمَّ إِنَّا نَسْأَلُكَ فِي سَفَرِنَا هَذَا الْبِرَّ وَالتَّقْوَى، وَمِنَ الْعَمَلِ مَا تَرْضَى، اللَّهُمَّ هَوِّنْ عَلَيْنَا السَّفَرَ، وَاطْوِ عَنَّا بُعْدَهُ، اللَّهُمَّ أَنْتَ الصَّاحِبُ فِي السَّفَرِ، وَالْخَلِيفَةُ فِي الْأَهْلِ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ وَعْثَاءِ السَّفَرِ، وَكَآبَةِ المنظر، وسوء الْمُنْقَلَبِ فِي الْمَالِ وَالْأَهْلِ..» .

"አላሁ አክበር አላሁ አክበር አላሁ አክበር ከዚያም እንዲህ ይበል: {ሱብሓነልለዚ ሰኸኸረ ለና ሀዛ ወማ ኩና ለሁ ሙቅሪኒን ወኢና ኢላ ረቢና ለሙንቀሊቡን} [አዝዙኽሩፍ:14] አልላሁመ ኢንና ነስአሉከ ፊ ሰፈሪና ሀዛ አልቢርረ ወትተቅዋ፣ ወሚነል ዐመሊ ማ ተርዷ፣ አልላሁመ ሀውዊን ዐለይና ሰፈረና ሀዛ፣ ወጥዊ ዓና ቡዕደሁ፣ አልላሁምመ አንተሰ -ሷሒቡ ፊ ሰፈር፣ ወልኸሊፈቱ ፊልአህል፣ አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ወዕሣኢ(14) ሰፈር፣ ወከኣበቲል መንዘር፣(15) ወሱኢል ሙንቀለብ(16) ፊልማሊ ወልአህል (17) ..." (ትርጉሙም: አላህ ታላቅ ነው። አላህ ታላቅ ነው። አላህ ታላቅ ነው። እኛ የማንችለው ሆነን ሳለ ይህንን ለኛ ያገራልን ጌታ ጥራት ይገባው። እኛም ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን። አላህ ሆይ! እኛ በዚህ ጉዟችን በጎን ነገርና ፍራቻን፣ ከስራም የምትወደውን እንጠይቅሃለን። አላህ ሆይ ይህንን ጉዟችንን አቅልልልን፣ ርቀቱንም ሰብስብልን። አላህ ሆይ! እኛን በጉዟችን የምትጎዳኘን፣ በቤተሰቦቻችን ጉዳይም የምትተካን አንተው ነህ። አላህ ሆይ! እኔ ከጉዞ መከራ፣ መጥፎ በሆነ ገፅታ ከመታየትና ወደ ቤተሰቦቼና ንብረቶቼ መጥፎ አመላለስን ከመመለስ በአንተ እጠበቃለሁ።) ማለት ነው።

---

(13) ወዕሣኢ-ስ-ሰፈር ማለት: የጉዞ መከራ ማለት ነው። አልኢፍሷሕ ዐን መዓኒ ሲሓሕ (4/284)

(14) ("ከአበቲል መንዘር" የተባለው): መጥፎ ገፅታ፣ በሀዘን የተጎሳቀለ ማንነት ማለት ነው። አልኢፍሷሕ ዐን መዓኒ ሲሓሕ (4/284)

(15) (አልሙንቀሊብ) ማለት መመለስ ማለት ነው። አልኢፍሷሕ ዐን መዓኒ ሲሓሕ (4/284)

(16) ኢማሙ አሕመድ በሙስነዳቸው በቁጥር (6374 ዘግበውታል

(17) ቡኻሪ በቁጥር (2998) ዘግበውታል



## 14 ያለ ጓደኛ ብቻውን ባይጓዝ ይመረጣል።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው:

«لَوْ يَعْلَمُ النَّاسُ مَا فِي الْوَحْدَةِ مَا أَعْلَمُ مَا سَارَ رَاكِبٌ بِلَيْلٍ وَحْدَهُ».

«ሰዎች በብቸኝነት ውስጥ ያለውን (ጉዳት) እኔ የማውቀውን ያህል ቢያውቁ ኖሮ፣ ማንም ጋላቢ በሌሊት ብቻውን አይጓዝም ነበር።»[18]

(18) አቡ ዳውድ በቁጥር (2608) ዘግበውታል

# 15

## ተጓዦች ከመካከላቸው አንዱን መሪያቸው አድርገው ይሹሙ፤

ይህም አንድነታቸውን ይበልጥ የሚሰበስብ፣ ለስምምነት ይበልጥ የሚያመች፣ እንዲሁም ዓላማቸውን ለማሳካት የሚያጠናክር በመሆኑ ነው።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል:

«إِذَا خَرَجَ ثَلَاثَةٌ فِي سَفَرٍ فَلْيُؤَمِّرُوا أَحَدَهُمْ».

**(ሶስት ሰዎች ለጉዞ ከወጡ አንዱን መሪያቸው ያድርጉ!)** (19)

(19) ኢማሙ አሕመድ በሙስነዳቸው በቁጥር (17736) ዘግበውታል



**16**

አላህ በርሱ ላይ ግዴታ ያደረገበትን አምልኮ ለመወጣት፣ ክልክሎችን ለመራቅ፣ የላቀ ስነምግባርን ለመላበስ፣ እገዛውንና እርዳታውን የሚፈልግ ሰውን ለማገዝ፣ እውቀትን ለሚፈልግ ሰው እውቀትን ለመስጠት ጉጉት ሊኖረው ይገባል።

በገንዘቡም ቸር መሆን ይገባዋል። ገንዘቡን ለነፍሱ ጥቅምና ለወንድሞቹ ጥቅምና ፍላጎት ፈሰስ ማድረግ ይገባዋል።

**17**

መንገድ በወጣበት ያላሰበው ጉዳይ አጋጥሞት ነገሮች ሊወሳሰቡበት ስለሚችሉ የጉዞ በጀቱንና ስንቁን ማብዛት ይገባዋል።



**18**

እነዚህን ሁሉ ሲፈፅምም የሚለመድና የሚላመድ ሰው እንዲሆን ፊቱን ፈታ አድርጎ፣

ነፍሱ ተደስታና ጓደኞቹንም ደስተኛ ለማድረግ እየጣረ መፈፀም ይገባዋል።

## 19 ከጓደኞቹ ለሚያጋጥመው ሻካራ ባህሪና የሐሳብ አለመስማማት በትዕግስት ሊያልፍ ይገባል።

እንዲሁም በመካከላቸው የተከበረና በልባቸውም ከፍ ያለ ቦታ እንዲኖረው፣ በተሻለችው መንገድ ሊይዛቸው ይገባል።

## 20 ተጓዦች አንድ ስፍራ ላይ እረፍት ሲወስዱ እርስ በርሳቸው ተጠጋግተው መቀመጥ ይወደድላቸዋል።

የተወሰኑ ሶሓቦች አንድ አካባቢ ላይ ሲያርፉ ወደ ሸለቆዎችና ወደ ተራራ ስር ተበታትነው ያርፉ ነበር።

ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሏቸው:

«إِنَّ تَفَرُّقَكُمْ فِي الشِّعَابِ وَالْأَوْدِيَةِ إِنَّمَا ذَلِكُمْ مِنَ الشَّيْطَانِ»

**«ይህ ወደ ሸለቆና ወደ ተራራ ስር ተበታትናችሁ ማረፋችሁ ከሸይጧን ነው።»[20]**

ከዛን ጊዜ በኋላ ልብስ ቢዘረጋላቸው ሁሉንም በቅቷቸው በሚያስቀምጥ ደረጃ እርስ በርሳቸው ተጠጋግተው ይቀመጡ ነበር።

## 21 ከጉዞም ይሁን ከሌላ ቦታ ወደ አንድ ስፍራ በሚያርፍ ወቅት ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ተረጋግጦ የመጣውን ዱዓ ማድረጉ ይወደድለታል:

ሙስሊም በቁጥር (2708) ዘግበውታል

«أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ»؛

(አዑዙ ቢከሊማቲላሂ አትታማት ሚን ሸሪ ማ ኸለቅ) ትርጉሙም (ከፍጡራኑ ክፋት ሙሉ በሆኑ የአላህ ቃላት እጠበቃለሁ።) ማለት ነው።[21]

እርሱ ይህንን ካለ ከዛ ስፍራ ለቆ እስኪንቀሳቀስ ድረስ ምንም ጉዳት አያገጥመውም።

## 22 ከፍ ወዳሉ ቦታዎች ላይ ሲወጣ ተክቢራ ማለት፣ ዝቅ ወዳሉ ስፍራዎችና ወደ ሸለቆ ሲወርድ ደግሞ ተስቢሕ ማለቱ ይወደድለታል። ጃቢር (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) እንዲህ ብሏል:

«ከፍ ወዳሉ ቦታዎች ስንወጣ ተክቢራ፣ ስንወርድ ደሞ ተስቢሕ እንል ነበር።»[22]

ተክቢር በሚሉበት ወቅትም ድምፅን ከፍ ማድረግ አይገባም። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል:

«يَا أَيُّهَا النَّاسُ ارْبَعُوا عَلَى أَنْفُسِكُمْ فَإِنَّكُمْ لَا تَدْعُونَ أَصَمَّ وَلَا غَائِبًا إِنَّهُ مَعَكُمْ إِنَّهُ سَمِيعٌ قَرِيبٌ».

(እናንተ ሰዎች ሆይ! ለነፍሳችሁ እዘኑ። እናንተ የምትጠሩት ደንቆሮንም ሆነ ሩቅ የሆነን አይደለምና። እርሱ ከእናንተ ጋር ነው፤ እርሱ ሰሚ፤ ቅርብ ነው።)[23]

## 23 ከሚጓዝባቸው ወቅቶች መካከል ምሽት ላይ በተለይም በምሽቱ መጀመሪያ ላይ ጉዞ ቢያደርግ ይወደድለታል። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው:

(21) ቡኻሪ በቁጥር (2994) ዘግበውታል
(22) ቡኻሪ በቁጥር (2993) ዘግበውታል
(23) አቡ ዳውድ በቁጥር (2571) ዘግበውታል

«عَلَيْكُمْ بِالدُّلْجَةِ؛ فَإِنَّ الْأَرْضَ تُطْوَى بِاللَّيْلِ».

**«የምሽት ጉዞን አደራ ተጓዙ። ምድር በምሽት ትሰበሰባለችና።»**[24]

## 24 በጉዞ ወቅት ዱዓ ማብዛት ይወደድለታል።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው:



«ثَلَاثُ دَعَوَاتٍ مُسْتَجَابَاتٌ لَا شَكَّ فِيهِنَّ: دَعْوَةُ الْمَظْلُومِ، وَدَعْوَةُ الْمُسَافِرِ، وَدَعْوَةُ الْوَالِدِ عَلَى وَلَدِهِ».

**«ተቀባይነታቸው ጥርጥር የሌለባቸው ሦስት ዱዓዎች አሉ፦ የተበዳይ ዱዓ፣ ጉዞ ላይ ያለ ሰው የሚያደርገው ዱዓና ወላጅ ለልጁ የሚያደርገው ዱዓ ናቸው።»**[25]

(24) ኢማሙ አሕመድ በሙስነዳቸው በቁጥር (10771) ዘግበውታል

(25) ኢማሙ አሕመድ በሙስነዳቸው በቁጥር (10068) ዘግበውታል

# ሁለተኛ: የጠሀራ አፈፃፀም በጉዞ ወቅት:

**ጉዞ ላይ ያለ ሰው ለጠሃራው ትኩረት መስጠት ግዴታው ነው።**

ትንሹ ሐደሥ ሲያጋጥመው ዉዱእ ያድርግ ጀናባ ሲያጋጥመው ደግሞ ገላውን ይታጠብ።

**ውሃ ካላገኘ ወይም ያለው ውሃ ለመብሉና ለመጠጡ የሚፈልገው ያህል ትንሽ ውሃ ብቻ ከሆነ ተየሙም ያድርግ።**



**የተየሙም አፈፃፀም:**

በሁለት እጆቹ መሬቱን ይመታ እና በነርሱ ፊቱንና መዳፎቹን ያብሳል።

**የተየሙም ጦሃራ ጊዜያዊ ጦሃራ ነው። ልክ ውሃ እንዳገኘ የተየሙሙ ጠሃራ ይበላሽና ውሃውን መጠቀሙ ግዴታው ይሆናል።**

ጀናባ አጋጥሞት ተየሙም ካደረገ በኋላ ከዚያም ውሃ ቢያገኛ ገላውን ታጥቦ ጀናባውን ማንሳት ግዴታው ይሆናል። ተፀዳድቶ ተየሙም ቢያደርግ እና ከዚያም ውሃ ቢያገኝ ዉዱእ ማድረግ ግዴታው ይሆናል።

በሐዲሥ እንዲህ የሚል ተዘግቧል:

«الصَّعِيدُ الطَّيِّبُ وَضُوءُ الْمُسْلِمِ وَإِنْ لَمْ يَجِدِ الْمَاءَ عَشْرَ سِنِينَ، فَإِذَا وَجَدَ الْمَاءَ فَلْيَتَّقِ اللهَ، وَلْيُمِسَّهُ بَشَرَتَهُ».

**"አንድ ሙስሊም ለአስር አመት ውሃ ባያገኝ እንኳ ንፁህ አፈር የሙስሊም ዉዱእ ማድረጊያ (ሆኖ የሚቆጠር) ነው። ውሃ ያገኘ ጊዜ ግን አላህን ይፍራ! ሰውነቱን በውሃ ያስነካው።"** (26)


- **በሁለት ኹፎች ላይ ማበስ በቁርአን፣ በሐዲሥና በአህሉ ሱና ዑለሞች ስምምነት ባጠቃላይ የተደነገገ ነው።**

- **በሁለት ኹፎች ላይና በነርሱ ተመሳሳይ ብይን ያለው ነገር ላይ ለማበስ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው:**

**1.** ኹፎቹ ወይም ካልሲዎቹ ንፁህና ፍቁድ መሆን አለባቸው፤

**2.** ዉዱእ ያለው ሆኖ ሊለብሳቸው ይገባል፤

**3.** ኹፎቹ ዉዱእ ሲያደርግ የግዴታ ማጠብ የሚገባውን የእግር ክፍል የሚሸፍኑ መሆን አለባቸው፤



(26) ቡኻሪ በቁጥር (1804) እና ሙስሊም በቁጥር (1927) ዘግበውታል

**4.**

የሚያብሰው ትንሹ ሐደሥ ሲያጋጥመው ብቻ መሆን አለበት። ጀናባን ወይም ገላ መታጠብን የሚያስገድዱ ነገሮች ሲያጋጥሙት ኹፋ ላይ ማበስ አይፈቀድለትም።

**5.**

የሚያብሰውም በሸሪዓ በተገደበለት ወቅት ውስጥ መሆን አለበት። እርሱም ሀገሩ ተቀማጭ ለሆነ ሰው አንድ ቀን ከነሌሊቱ ሲሆን ጉዞ ላይ ላለ ሰው ደግሞ ሶስት ቀን ከነሌሊቱ ነው። ይህ የጊዜ ገደብ የሚጀምረውም በትክክለኛው የዑለሞች አቋም መሰረት ዉዱእ ካጠፋ በኋላ መጀመሪያ ማበስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሀገሩ ተቀማጭ የሆነ ሰው ልክ በሃያ አራተኛ ስአቱ ጊዜ ገደቡ ሲጠናቀቅበት ጉዞ ላይ ያለ ሰው ደግሞ ልክ በሰባ ሁለተኛ ስአቱ ይጠናቀቅበታል።



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

## የማበስ ፈቃዱ ከሶስት ነገሮች መካከል አንዱ ከተከሰተ ይበላሻል:

1. ጀናባን የመሰለ ገላ መታጠብን የሚያሰገድድ ነገር ከተከሰተ የግድ መታጠብ ሰላለበት የማበስ ፍቃዱ ይበላሻል።

2. ካበሰ በኋላ ካወለቃቸው፤

3. በሸሪዓ የተገደበው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀም የማበስ ፍቃዱ ይበላሻል።

* * *



ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# ጉዞ ላይ ሶላትን የማሳጠር ህግጋት፡

## ጉዞ ላይ ሞልቶ ከመስገድ ይልቅ አሳጥሮ መስገድ በላጭ ነው።

ነገር ግን ጉዞ ላይ ያለ ሰው ባለ አራት ረከዓ ሶላቶችን አራት ረከዓ አድርጎ ሞልቶ ቢሰግድ ሶላቱ ትክክለኛ ናት። ይሁን እንጂ በላጭ የሆነውን ተቃርኗል።

## ጉዞ ላይ ያለ ሰው በሚኖርበት መንደር ወይም ከተማ ካሉ አጠቃላይ ቤቶች አልፎ ሲወጣ ማሳጠር ይችላል።

ይህም የአብዛኛው ዑለማዎች አቋም ነው።



የሶላት ወቅት ከገባ በኋላ ቢጓዝ ወቅቱ ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ ጉዞ የጀመረው ማሳጠር ይችላል።

ጉዞ ላይ ያለ ሰው በሚያስፈልገው ወቅት

በዝሁርና በዐስር

መካከል፣

በመግሪብና በዒሻ

መካከል ሰብስቦ መስገዱ ሱና ነው። ጉዞውን ሳያርፍ እየገሰገሰ ከቀጠለ አስቀድሞ ወይም አዘግይቶ ለርሱ ምቹ በሆነው ወቅት ሰብስቦ ይሰግዳል።



### ሰብሰቦ መስገዱ ጉዞ ላይ ላለው ሰው አስፈላጊ ካልሆነ በቀር (በየወቅቱ ነጣጥሎ እንጂ) ሰብሰቦ አይሰገድ።

ለምሳሌ አንድ ሰፍራ ላይ አርፎ የሁለተኛው ሶላት ወቅት ከገባ በኋላ እንጂ መንቀሳቀስ በማይፈልግበት ሁኔታ ላይ ከሆነ በላጩ ሰብሰቦ አለመስገዱ ነው። ምክንያቱ ደግሞ መሰብሰቡ ምንም ስለማያስፈልገው ነው። ለዛም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመሰናበቻ ሐጅ ወቅት ሚና ባረፉ ጊዜ ስላላስፈለጋቸው ሰብሰበው አልሰገዱም።

## ሱና ሶላቶችን በተመለከተ

ጉዞ ላይ ያለ ሰው ሀገሩ የተቀመጠ ሰው የሚሰግደውን ሱና ሶላቶች ይሰግዳል። የዱሓ ሶላትን፣ የለይልና የዊትር ሶላትን ሌሎችንም ከዝሁር፣ ከመግሪብና ከዒሻ ቀብሊያና ባዕዲያ ሶላት ውጪ ያሉ ሱና ሶላቶችን መስገድ ይችላል። ከፈጅር ቀብሊያ ውጪ ያሉ ቀብሊያና በዕዲያ ሶላቶችን ግን ሱናው አለመስገዱ ነው።

### ጉዞ ላይ እንደፕሌን፣ መኪና፣ መርከብና ሌሎችም መጓጓዣዎች ላይ ሱና ሶላቶችን መስገድ ይፈቀዳል።

ግዴታ ሶላት ከሆነ ግን ከአቅሙ በላይ እስካልሆነ ድረስ የግድ መውረድ ይኖርበታል።



# ጉዞ ላይ የሆነ ሰው ሀገሩ ተቀማጭ ከሆነ ሰው ኋላ መስገዱ ይበቃለታል።

ነገር ግን ጉዞ ላይ ያለው ሰው ከኢማሙ ጋር አብሮ ለመስገድ ያገኘው ሁሉንም ረከዓ ይሁን ወይም አንድ ረከዓና ከዛ በታች ቢሆንም ኢማሙ የመጨረሻው ተሸሁድ ላይ እያለ ከማስላመቱ በፊት ቢጀምር እንኳ ልክ እንደ ኢማሙ ሶላቱን ሞልቶ ነው የሚሰግደው። ከዑለሞች ሁለት የተለያዩ አቋሞች መካከል ትክክለኛውና ሚዛን የሚደፋው ይሄ ነው።

## አራተኛ፡ ከሐጅ፣ ከዑምራ ወይም ከጉዞ የመመለስ ስነስርዓት፡

### ለመመለስ መፍጠን ይገባዋል። ያለአስፈላጊ ጉዳይ ጉዞ ላይ መቆየት አይገባውም።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው:

«السَّفَرُ قِطْعَةٌ مِنَ الْعَذَابِ، يَمْنَعُ أَحَدَكُمْ طَعَامَهُ وَشَرَابَهُ وَنَوْمَهُ، فَإِذَا قَضَى نَهْمَتَهُ فَلْيُعَجِّلْ إِلَى أَهْلِهِ».

«ጉዞ ከስቃይ አንዱ ቁራጭ ነው። ከእናንተ አንዱን ምግብ፣ መጠጥና እንቅልፉን (በስርዓቱ እንዳያገኝ) ይከለክለዋል። ስለዚህ፣ የጉዞ ዓላማውን ከፈጸመ፣ ፈጥኖ ወደ ቤተሰቡ ይመለስ።»[27]

### ወደ ሃገሩ መመለስ በፈለገ ጊዜ መጓጓዣው ላይ እንደወጣ የጉዞን ዱዓ

ይቅራና ይህንን ይጨምርበት:

«آيِبُونَ تَائِبُونَ عَابِدُونَ لِرَبِّنَا حَامِدُونَ».

«አዩቡን፣ ታኢቡነ፣ ዐቢዱነ ሊረቢና ሓሚዱን) ትርጉሙም (ተመላሾች ነን፣ ተፀፃቾች ነን፣ ጌታችንን አምላኪዎችና አመስጋኞች ነን።»[28]

---

(27) ቡኻሪ በቁጥር (1797) እና ሙስሊም በቁጥር (1342) ዘግበውታል

(28) ቡኻሪ በቁጥር (4116) ዘግበውታል

## ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጉዞ በሚመለሱ ወቅት እንደሚሉ የተረጋገጠውን ውዳሴ ከጉዞ በሚመለስ ወቅት ማለቱ ይወደዳል። እርሳቸው ከዘመቻ ወይም ከሐጅ ወይም ከዑምራ በሚመለሱ ወቅት ከፍ ያለ ቦታ ላይ በወጡ ቁጥር ሶስት ጊዜ ተክቢራ ይሉ እና ቀጥለውም እንዲህ ይሉ ነበር :

«لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ، وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، آيِبُونَ، تَائِبُونَ، عَابِدُونَ، سَاجِدُونَ، لِرَبِّنَا حَامِدُونَ، صَدَقَ اللهُ وَعْدَهُ، وَنَصَرَ عَبْدَهُ، وَهَزَمَ الْأَحْزَابَ وَحْدَهُ».

(ላኢላሃ ኢለሏሁ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ፣ ለሁልሙልኩ፣ ወለሁል ሐምዱ፣ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፣ አዪቡነ ታኢቡነ ዐቢዱነ ሳጂዱነ ሊረቢና ሓሚዱን፣ ሰደቀሏሁ ወዕደህ፣ ወነሶረ ዐብደህ፣ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደህ) ትርጉሙም (ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም፤ ብቸኛና አጋር የለውም። ንግስና ለርሱ የተገባ ነው። ምስጋናም ለርሱ የተገባ ነው። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው። ተመላሾች፣ ተፀፃቾች፣ አምላኪዎች፣ ሰጋጆች፣ ለጌታችን አመስጋኞች ነን። አላህ ቃሉን በእውነት ሞላ፣ ባሪያውንም ረዳ፣ የጥመት ጭፍራንም ብቻውን አሸነፈ።)[29]



(29) ቡኻሪ በቁጥር (1797) እና ሙስሊም በቁጥር (1342) ዘግበውታል

## ሀገሩን በተመለከተ ወቅት እንዲህ ማለቱ ይወደድለታል:

«آيِبُونَ تَائِبُونَ عَابِدُونَ لِرَبِّنَا حَامِدُونَ»،
"ኣይቡነ፤ ታኢቡነ፤ ዓቢዱን ሊረቢና ሐሚዱን" (ትርጉሙም: ጌታችንን እያመሰገንን ተፀፃቾችና፤ ተውባ አድራጊዎች፤ ሆነን ተመለስን።)[30]

ይህንንም ሀገሩ እስኪገባ ድረስ ይደጋግመው። ይህም የሚያደርገው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ስለፈፀሙት ነው።

## ከቤተሰቡ ለረጅም ጊዜያት ርቆ ሲመለስ አስፈላጊ ሁኖ ወይም በምሽት እንደሚደርስ ቀድሞ አሳውቋቸው ካልሆነ በቀር በምሽት አይግባ።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ስለከለከሉ ነው። ጃቢር ቢን ዐብደላህ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ:

«نَهَى رَسُولُ اللهِ صلى الله عليه وسلم أَنْ يَطْرُقَ الرَّجُلُ أَهْلَهُ لَيْلًا»،
"ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ሰውዬው ወደ ቤተሰቡ በምሽት መግባቱን ከለከሉ።" [31]

የዚህንም ጥበብ ሌላኛው ዘገባ እንዲህ በሚል አብራርቶታል:

«حَتَّى تَمْتَشِطَ الشَّعِثَةُ، وَتَسْتَحِدَّ الْمُغِيبَةُ»،[32]
(ፀጉሯ ቅባት ሳይነካው ከርሞ የተንጨባረረባት እንድታበጥር፣ ባሏ ርቆ የከረመባት (የምትላጨውን) እንድትላጭ ነው።)[33]

---

(30) ሙስሊም በቁጥር (715) ዘግበውታል
(31) (ሸዕሣ) ማለት ፀጉሯ ቅባትና መበጠርን ካየ ጊዜያትን ያስቆጠረች ማለት ነው። (ኢስቲሕዳድ) ማለት ስለትን ለመላጨት መጠቀም ማለት ነው። (ሙገየባህ) ማለት ባሏ ከርሷ የራቀ ማለት ነው። "አትተሕሪር ፊ ሸርሒ ሶሒሕ ሙስሊም - አልአስበሃኒይ" (292 ገፅ)
(32) ነሳኢይ በቁጥር (9099) ዘግበውታል
(33) ሙስሊም በቁጥር (715) ዘግበውታል

በሌላ ዘገባ ደግሞ

«نَهَى رَسُولُ الله صلى الله عليه وسلم أَنْ يَطْرُقَ الرَّجُلُ أَهْلَهُ لَيْلًا، يَتَخَوَّنُهُمْ أَوْ يَلْتَمِسُ عَثَرَاتِهِمْ».

«የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) አንድ ሰው ቤተሰቦቹን በክህደት ለመጠርጠር ወይም ነውራቸውን ለመሰለል አስቦ በሌሊት (ድንገት) መምጣቱን ከልክለዋል።»[34]

## ከጉዞ ወደ ሃገሩ የሚገባ ሰው በቅድሚያ ቤቱ አካባቢ የሚገኝ መስጂድ በመግባት ሁለት ረከዐ ይሰገድ።

ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ስለፈፀሙት ነው።



(34) ሙስሊም በቁጥር (2428) ዘግበውታል

## አንድ ጉዞ የወጣ ሰው ከጉዞው ሲመለስ የራሱና የጎረቤቱ ልጆች አቀባበል ሲያደርጉለት እዝነት ሊያሳያቸውና በጎ ነገር ለነርሱ ማድረጉ ይወደድለታል።

ከኢብኑ ዐባስ (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) መካ የገቡ ጊዜ የበኒ ዐብዱል ሙጦሊብ ህፃናቶች አቀባበል አደረጉላቸው። ከህፃናቶቹ መካከልም አንዱን ከፊታቸው አንዱን ከኋላቸው ተሸከሙ።» ዐብደላህ ቢን ጀዕፈር (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) እንዲህ አሉ:

> "كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى الله عليه وَسَلَّمَ إِذَا قَدِمَ مِنْ سَفَرٍ تُلُقِّيَ بِنَا، قَالَ: فَتُلُقِّيَ بِي وَبِالْحَسَنِ أَوْ بِالْحُسَيْنِ، قَالَ: فَحَمَلَ أَحَدَنَا بَيْنَ يَدَيْهِ وَالْآخَرَ خَلْفَهُ حَتَّى دَخَلْنَا الْمَدِينَةَ".
>
> «ነብዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጉዞ ሲመለሱ እኛ (ልጆች) እየወጣን እንቀበላቸው ነበር። እኔና ሐሰን ወይም ሑሰይን ልንቀበላቸው ወጥተን ነበር፤ እሳቸውም አንዳችንን ከፊትለፊታቸው፣ ሌላኛችንን ደግሞ ከኋላቸው (በእንስሳቸው ላይ) አንግበው (አፈናጠው) መዲና እስክንገባ ድረስ ይዘውን ገቡ።»[35]

## ስጦታ መስጣጠት ልብን ስለሚያፋቅር፣ መቃቃርን ስለሚያስወግድ ይወደዳል። መቀበሉና የስጦታውን ውለታ መመለስም ይወደዳል።

ስጦታውን ከመቀበል የሚከለክለው ሸሪዓዊ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ስጦታውን መመለስ ይጠላል። ለዚህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል:

> «تَهَادُوا تَحَابُّوا».
>
> «ስጦታ ተስጣጡ፤ ትዋደዳላችሁ።»[36]

---

(35) አል'በይሃቂይ በ«አስ-ሱነኑ አል-ኩብራ» (11946) ዘግበውታል

(36) ጦበራኒይ በ"አልአውስጥ" በቁጥር (97) ዘግበውታል

በሙስሊሞች መካከል ውዴታን ከሚያመጡ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው።



## አንድ ጉዞ የወጣ ሰው ወደ ሃገሩ የገባ ጊዜ በመተቃቀፍ ሰላምታ መለዋወጡ ይወደድለታል።

ይህም ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባልደረቦች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። አነሰ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) እንዲህ አለ:

> «በሚገናኙበት ወቅት በመጨባበጥ ሰላምታ ይለዋወጡ ነበር። ከጉዞ የገቡ ጊዜ ግን በመተቃቀፍ ነበር ሰላምታ የሚለዋወጡት።»[37]

**የአሏህ ሶላትና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ ላይ ይስፈን።**

---

(37) ቡኻሪ በቁጥር (3116) እና ሙስሊም በቁጥር (100) ዘግበውታል

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

# ማውጫ


የጉዞ ስነስርዓትና ህግጋቶቹ ........ 3

የመጀመሪያው: የጉዞ ስነስርዓት ........ 4

ሁለተኛ: የጠሀራ አፈፃፀም በጉዞ ወቅት: ........ 18

ጉዞ ላይ ሶላትን የማሳጠር ህግጋት: ........ 22

አራተኛ: ከሐጅ፣ ከዑምራ ወይም ከጉዞ የመመለስ ስነስርዓት: ........ 26

# تعرف على الإسلام

## بأكثر من 100 لغة

موسوعة الأحاديث النبوية
HadeethEnc.com

ترجمات متقنة للأحاديث النبوية وشروحها بأكثر من (60) لغة

بيان الإسلام
byenah.com

مواد منتقاة للتعريف بالإسلام وتعليمه بأكثر من (120) لغة

موسوعة القرآن الكريم
QuranEnc.com

ترجمات متقنة لمعاني القرآن الكريم بأكثر من (75) لغة

موسوعات وخدمات إسلامية باللغات
s.islamenc.com

للمزيد
من المواقع الإسلامية
بلغـــــات العـــــالم

جامع المحتوى الإسلامي باللغات
islamcontent.com

مواد إسلامية متنوعة وشاملة بأكثر من (125) لغة

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com

مواد منتقاة للحجـــاج
والمعتمرين و الزوار
بلغات العالم

جمعية خدمة المحتوى الإسلامي باللغات

ضيوف الرحمن
hajjumrh.com